# በሁመራ፣ በዳንሻ እና በቢሶበር ሲቪል ሰዎች ስለሚገኙበት ሁኔታ የተደረገ አጭር የክትትል ሪፖርት

## *መግቢያ*

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) ጦርነት በተካሄደባቸው የትግራይ ክልል እና አዋሳኝ አካባቢዎች ያለውን ሁኔታ፣ በቦታው ያሉ የሲቪል ሰዎችን ደኅንነት እንዲሁም በጦርነቱ ምክንያት ከመኖሪያ ቦታቸው የተፈናቀሉ ሰዎችን ሁኔታ በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡

ኮሚሽኑ ከኅዳር 5 እስከ ኅዳር 9 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ በዳንሻ፣ በሁመራ እና በማይካድራ ተዘዋውሮ ምርመራ ካደረገ ብኋላ፣ ለሁለተኛ ዙር የመስክ ምልከታ ከታኅሣሥ 6 እስከ ታኅሣሥ 11 ቀን 2013 ዓ.ም. ወደ ትግራይ እና አማራ ክልሎች ተጉዟል፡፡ በወቅቱ በተለይም በትግራይ ክልል የነበረው የፀጥታ ሁኔታ በክትትሉ እቅድ መሰረት ኮሚሽኑ ሊያካትታቸው ያሰባቸው አካባቢዎችን በሙሉ (ሁመራ፣ ማይካድራ፣ ዲማ፣ አዲ ጎሹ፣ ራውያን እና በረኸት) ለማካተት ባይችልም በጎንደር እና በዳንሻ በመገኘት በተለይም ከትግራይ ክልል የተፈናቀሉ ሰዎች የሚገኙበትን ሁኔታ ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላትና ኃላፊዎች ከማነጋገር በተጨማሪ በሆስፒታል እና በተለያዩ መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ተፈናቃዮችን፣ ተጎጂዎችን፣ በግጭቱ የተሳተፉ ሰዎችንና የህክምና ባለሞያዎችን አነጋግሮ መረጃ ሰብስቧል፡፡

ከታኅሣሥ 22 እስከ ታኅሣሥ 27 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ ደግሞ በትግራይ ክልል፣ ደቡባዊ ዞን፣ ጨርጨር ወረዳ በሚገኙት ኡላጋ እና ቢሶበር መንደሮች በመጓዝ ከኅዳር 5 እስከ ኅዳር 8 ቀን 2013 ዓ.ም.  ድረስ በአካባቢው ስለደረሰ የሲቪል ሰዎች ሕይወት መጥፋት፣ የአካል ጉዳት መድረስ እና የንብረት መዘረፍና መውደም ማጣራት አድርጓል፡፡ በተጠቀሱት ቦታዎች በመዘዋወር ተጎጂዎችን፣ የተጎጂ ቤተሰቦችን፣ ምስክሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት አነጋግሯል፡፡

የኮሚሽኑ ባለሞያዎች ከጥር 2 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ለተጨማሪ ዙር የመስክ ምልከታ ወደ መቀሌ ከተማ እና ሌሎች የትግራይ ክልል አካባቢዎች በመንቀሳቀስ በግጭቱ ምክንያት የተፈጠረውን የሰብአዊ ቀውስ እና የሰብአዊ መብት ጉዳዮች በመመርመር ላይ የሚገኝ ሲሆን ስራው እንደተጠናቀቀ ሙሉ ሪፖርቱን ይፋ የሚደረግ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

## *ሁመራ*

ሁመራ ከመቀሌ በ500 ኪ.ሜ ርቀት እና ከጎንደር 252 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የሚገኝ አካባቢ ሲሆን፣ የሕዝብ ቁጥሩ ከ40 ሺህ በላይ እንደሚደርስ ይገመታል፡፡

በጦርነቱ ወቅት በሁመራ ለ3 ቀናት ገደማ የቆየ ከፍተኛ ውግያ የነበረ ሲሆን፣ የከባድ መሳርያ እና የተኩስ ድምጽ ይሰማ ነበር፡፡ ተኩሱ በአንዳንድ የሁመራ መንደሮች ንብረቶችና መሰረታዊ ልማቶች ላይ ያደረሰውን ጉዳት ኢሰመኮ ተመልክቷል፡፡ ይሁንና በተለይም ቀበሌ 2 በተባለው መንደር ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን የሚያመላክቱ መረጃዎች ቢደርሱትም፣ የኮሚሽኑ ቡድን ሁኔታውን በምልከታ ለማረጋገጥ አልቻለም፡፡ በቀበሌ 2 (ኩዳር በሚባል አካባቢ) መንደር ውስጥ በሚገኙት የቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን እና አንድ መስጊድ አካባቢ  ከጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ለሦስት ቀናት የቆየ

ከፍተኛ የከባድ መሳሪያ ድብደባ ነበር። በድብደባው የተጎዳው በተለይ   በቀበሌ 2 የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች እና ሕዝብ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ናቸው።  የኮሚሽኑ ባለሞያዎችም በሆስፒታሉ ላይ የደረሰውን ጉዳት መመልከት ችለዋል።

የትግራይ ልዩ ኃይልና የመከላከያ ሠራዊት አባላትን ጨምሮ  92 ሰዎች መሞታቸውን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የሁመራ ሆስፒታል ሰራተኛ ይናገራሉ። ኮሚሽኑ ይህንኑ መረጃ ከሌሎች ምንጮች ማጣራት አልቻለም። አንዳንዶቹ የህክምና እርዳታ ሲደረግላቸው ቆይተው በሆስፒታሉ የሞቱ መሆናቸውን የሆስፒታሉ ሰራተኛ አክለው ገልጸዋል። በጣም በርካታ ሰዎች (የሆስፒታሉን ሰራተኞች ጨምሮ) አካባቢውን ለቅቀው ተሰደዋል። የህክምና እርዳታ ከተሰጣቸው ሰዎች መካከል በቦምብ ፍንጣሪ ተጎድተው የቆሰሉ ሲቪል ሰዎች ይገኙበታል። የኮሚሽኑ የምርመራ ቡድን በሁመራ ሆስፒታል ከባለቤታቸው እና ከልጃቸው ጋር መሸሽ ያልቻሉና በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት በሆስፒታል ሲረዱ የነበሩ የሽመገሉ አባት አነጋግሯል። በቦምብ ፍንጣሪ ተመትተው በመጎዳታቸው ከአልጋ መንቀሳቀስ እንዳልቻሉና፣ ከ3 ቀናት ብኋላ ሰው አግኝቶ የህክምና እርዳታ እስኪያገኙ ድረስ በአሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ እንደቆዩ ገልጸዋል። ከጥቂት ቀናት በኋላ በሁመራ ሆስፒታል  በቂ እርዳታ ለማግኘት ባለመቻላቸው ወደ አብራጂራ መወሰዳቸው ተገልጿል። በአጠቃላይ ጦርነቱ ሲቪል ሰዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳደረሰ እንደሚያምኑ ባለሞያው ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

ሁመራ ከተማ ውስጥ “ፋኖ” በሚል ስም የሚንቀሳቀሱ ወጣት ወንዶች፣ አንዳንድ የአማራ ልዩ ኃይል አባሎች፣  የተወሰኑ የሚሊሻና የመከላከያ ሠራዊት አባላት እንዲሁም የኤርትራ ወታደሮች ጭምር በመኖሪያ ቤቶችና የንግድ ቤቶች ላይ ዝርፊያ ማካሄዳቸውን የከተማዋ ነዋሪዎች ይናገራሉ።  ዘራፊዎቹ የተከማቸ እህል ጭምር እንደወሰዱ፣ እንዲሁም በሁመራ በሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ላይ ስድብና ጥቃት እንዳደረሱ  የኮሚሽኑ ቡድን ከተለያዩ አካላት መረጃ ደርሶታል። አንድ የሁመራ ነዋሪ እንዳስረዱት “በርካታ ሰዎች፣ አንዳንዶች በአዲሱ አስተዳደር ለስራ የተሰማሩ ሰዎች ጭምር በዘረፋው ተሳትፈዋል። በአጠቃላይ ከግል ህሊና በስተቀር ፍትሕ የሚሰጥ ወይም የሚዳኝ አካል የለም” ሲሉ በምሬት ገልጸዋል። በአንጻሩ ሌሎች የሁመራ ነዋሪዎች ከፀጥታ ችግሩ ጋር ተያይዘው የመጡ ወንጀሎችን ለማስቀረት በቂ  የሚባል ባይሆንም የአማራ ልዩ ኃይል እና ሚሊሻ የፀጥታ ማስከበር እርምጃዎችን እየወሰዱ እንደነበረና ለምሳሌ ከምሽቱ 12:00 ሰዓት በኋላ የመንቀሳቀስ ገደብ ወይም የሰዓት እላፊ መታወጁን ተናግረዋል። የሰዓት እላፊው ለተሽከርካሪዎች ከምሽቱ 12:00 ሰዓት፣ ለእግረኞች ከምሽቱ 1:00 ሰዓት ጀምሮ ቢሆንም  በተለይ በምሽት በቡድን የሚንቀሳቀሱ ወጣት ዘራፊዎች እንዳሉ ነዋሪዎች ይገልጻሉ።

የኮሚሽኑ የምርመራ ቡድን በሁመራ በነበረበት ቀናት የአማራ ልዩ ኃይል እና ሚሊሻ ለአካባቢው ጥበቃ እያደረጉ መሆናቸውንና በየቀጠናው ጊዜያዊ አስተዳደሮችን ለማቋቋም እየተሞከረ እንደነበር ተመልክቷል። በተለይም ኮሚሽኑ ከኅዳር 5 እስከ ኅዳር 9 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ ባደረገው ጉዞ፣ በሁመራ ከተማ ውስጥ በትግራይ ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ ብሔር ተኮር  ማጉላላት (harassment) እንደነበረ ከተለያዩ ሰዎች ተረድቷል። ለምሳሌ አንድ የሁመራ ሆስፒታል ሰራተኛ፣ ሌሎች ሰዎች አካባቢውን ጥለው ቢሄዱም ሕይወታቸውን አደጋ ላይ በመጣል በሆስፒታሉ ሲያገለግሉ እንደቆዩና በአንድ ወቅት እስከ 7 ኪ.ሜ. የሚጠጋ መንገድ በእግራቸው በመመላለስ አገልግሎት ይሰጡ እንደነበር አስረድተው፤ በመንገዳቸው ላይ በብሔራቸው ምክንያት የተለያዩ እንግልቶች ይደርስባቸው እንደነበርና በአንድ ወቅት እንግልቱ ወደ አስጊ ደረጃ ሲያመራ የመከላከያ ሠራዊቱ አባላት ደርሰው እንዳስጣሏቸው ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

ኮሚሽኑ በሁመራ በተገኘበት ወቅት፣ በካሳዬ አበራ አጠቃላይ ሆስፒታል (ሁመራ ሆስፒታል) በቂ የህክምና ባለሞያዎች (ዶክተሮችና ነርሶች) እንዲሁም መድኃኒትና የህክምና ቁሳቁሶች አልነበሩም። አጠቃላይ ሆስፒታሉ  ከጦርነቱ በፊት 457 ሰራተኞች የነበሩት ቢሆንም፣ በኮሚሽኑ  ምልከታ ወቅት ከቀሩት አምስት ሰራተኞች ውስጥ አንዱ ብቻ ሃኪም ነበር። በውጊያው ወቅት በርካታ ታካሚዎች (የትግራይ ልዩ ኃይል፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትና፣ ሲቪል ሰዎችን ጨምሮ) በሆስፒታሉ የህክምና አገልግሎት ያገኙ ነበር። ሆስፒታሉ ጉዳት  የደረሰበት ከመሆኑ በተጨማሪም በአካባቢው የፀጥታ መደፍረስ ችግር የሆስፒታሉ መድኃኒቶችና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ተዘርፈው ነበር።

በአካባቢው  የምግብ አቅርቦት እጥረት ስለነበር የሁመራ ሆስፒታል ለታካሚዎቹ ምግብ አያቀርብም ነበር። የሆስፒታሉ ሰራተኞችም በእለት አንድ ቀን ብቻ እንደሚመገቡና ምግብ የሚያቀርቡላቸው ጎረቤቶቻቸው ወይም ቤት አከራያቸው መሆናቸውን ገልጸው ነበር።

በሁለተኛው የመስክ ምልከታ ኮሚሽኑ ወደ ሁመራ መጓዝ ባይችልም፣ በታኅሣሥ ወር አጋማሽ የደረሰው መረጃ ስጋት አድሮባቸው አካባቢውን ጥለው የሄዱ የሁመራ አጠቃላይ ሆስፒታል ባልደረቦች እየተመለሱ መሆናቸውንና 116 ሠራተኞች በስራ ገበታቸው ላይ መገኘታቸውን ተረድቷል። ከእነዚህም መካከል አምስት ሃኪሞች ፣ 12 ነርሶች፣ ሶስት አዋላጅ ነርሶች እና አንድ የጤና ኦፊሰር ይገኙበታል። ቀሪዎቹ የአስተዳደር እና የአጋዥ የስራ ዘርፍ አባላት ናቸው።

ይሁንና  በኮሚሽኑ ምርመራ ወቅት ሁመራ ከተማም ሆነ የሁመራ ሆስፒታል በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ።  የአካባቢው ነዋሪዎችና የሆስፒታሉ ሰራተኞች ለኢሰመኮ እንደገለጹት ‹‹የአካባቢው መሰረተ ልማት ባለመጠገኑና የባንኮች ወደ መደበኛ ስራቸው አለመመለስ የከተማዋ ነዋሪዎች ወደሌሎች አካባቢዎችና ወደ ሱዳን እንዲሰደዱ እያደረገ ነው። የሁመራ ነዋሪዎች ቁጥር እንደቀነሰ ማየት ይቻላል፣ የተወሰኑ ከሌሎች የትግራይ ክልል አካባቢዎች ለመመለስ ሙከራ ያደረጉ ነዋሪዎችም መኖሪያና ንግድ ቤቶቻቸው ባልታወቁ ሰዎች ተይዘው ስላገኙት ተመልሰው ሄደዋል። ከጥቂቶች በስተቀር ንግድ ቤቶች አልተከፈቱም፣ ትምህርትም አልተጀመረም። የከተማዋ ትራንስፖርት አገልግሎት ቀስ በቀስ እየተመለሰ ቢሆንም ዋጋው በሶስት እጥፍና ከዛ በላይ ጨምሯል። በሆስፒታሉ አቅራቢያ የሚኖሩ ነዋሪዎች ውሃ የሚያገኙት ከሆስፒታሉ የውሃ ማጠራቀሚያ ነው።”

የሆስፒታሉ ሰራተኞች ለኢሰመኮ የችግሩን አስከፊነት ሲገልጹ፡“የኤሌክትሪክና የውሃ አቅርቦት ባለመመለሱና በነዳጅ እጥረት ምክንያት የሆስፒታሉ ማቀዝቀዣዎችና መሳሪያዎችን ጥቅም ላይ ማዋል አዳጋች ሆኗል። አምቡላንሶች ለሌሎች ሰዎች ማጓጓዣ ሲውሉ አይተናል። የተወሰነ የምግብ እርዳታ ቢደረግም በቂ ባለመሆኑና በተለይም እስከ ጥር ወር ድረስ ደመወዝ አለመከፈሉ ሰራተኞቹን ለከፍተኛ የምግብ እጥረት አጋልጧል። በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ለአደጋ የሚያጋልጥ የጦር መሳሪያዎች መኖራቸው ይነገራል።  እኛ እርቦናል፣ በሶ እየበጠበጥን ነው የምንጠጣው። ግን ሰዎች እኛ ጋር ምግብ የሚያገኙ እየመሰላቸው ወደ እኛ ይመጣሉ። ለተደፈሩ ሴቶች የህክምና እርዳታ ሰጥተናል። አንድ ባልደረባችን በስራ ላይ እያለች በርሃብ ምክንያት እራሷን ስታለች፣ ይህን ሁሉ ችግር የተቋቋምነው ሆስፒታሉን ላለመዝጋት ነው፣ ሆስፒታል ስንውል ቤታችን ይዘረፋል፣ ሆስፒታሉን ለመጠበቅ በተራ በተራ ብናድርም ከመዘረፍ አላዳንነውም፣ በትግራይ ተወላጆች ላይ የሚያነጣጥሩ ስድቦች በሆስፒታሉ ግድግዳዎች ላይ ጭምር ተጽፈው እናገኛለን›› ብለዋል።

## ዳንሻ

የዳንሻ ወረዳ 31 የገጠር ቀበሌዎች እና 4 የከተማ ቀበሌዎች የያዘች፤ ከጎንደር ከተማ በ155 ኪ.ሜ.፣ ከሁመራ በ105 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የምትገኝ እና ለመጨረሻ ጊዜ በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ መሰረት ከ30 — 40 ሺህ  የሚገመት ሕዝብ የሚኖርባት ከተማ ናት።

ከታኅሣሥ 6 ቀን እስከ ታኅሣሥ 11 ቀን 2013 ዓ.ም. ኢሰመኮ ባደረገው ጉብኝት ፣ በዳንሻ ወረዳ በሲቪል ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱን የሚያመላክቱ መረጃዎች፣ ከጊዜያዊ የወረዳው አስተባባሪ፣ ከተጎጂዎች እና ከምስክሮች አግኝቷል። ነዋሪዎች በሲቪል ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱን፣ የደረሰው ጉዳት በግለሰቦች የእርስ በርስ ግጭት ሳይሆን “በጥይትና በፀጥታ ኃይሎች ተኩስ ልውውጥ” የደረሰ መሆኑን ያስረዳሉ። ይሁንና “በዚህ መልኩ የሞቱ ሰዎች በአካባቢው አለመቀበራቸውን፤ እንዲሁም ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ማንነት እና አድራሻ፣ የጉዳት መጠን፣ የተጎጂዎች ብዛት፣ ጾታ እና ተዛማጅ መረጃዎች በመጠናቀር ሂደት ላይ በመሆናቸው” የደረሰውን ጉዳት ግምት ለማወቅ አለመቻሉ ተገልጾ ነበር።  በሌላ በኩል  በጦርነቱ ወቅት 25 ሲቪል ሰዎች መገደላቸውን ኮሚሽኑ ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎች ቢደርሱትም፣ እነማን እንደሆኑና በየት አካባቢ እንደተቀበሩ ለማወቅ አልተቻለም።

ኮሚሽኑ ከኅዳር 5 እስከ ኅዳር 9 ቀን 2013 ድረስ ባደረገው ጉብኝት ወቅት፣ በዳንሻ ከሚገኘው የመከላከያ ሠራዊት አመራር አባላት በጦርነቱ ወቅት አስጨናቂ ሁኔታ እንደነበረ የተረዳ ቢሆንም፣

በሁለተኛው ዙር ምርመራው አካባቢው መረጋጋት መጀመሩን ተመልክቷል። መከላከያ ሠራዊቱ "ሕገ ደንቡንና የሥነምግባር መርኆዎችን በጠበቀ መልኩ እየተንቀሳቀሰ ስጋት ያደረባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ከሌሎች አካላት ጋር ተቀናጅቶ ጥበቃ ለማድረግ እየሞከረ እንደሆነ" አስረድቷል። "ስጋት ስላደረባቸው የተፈናቀሉ ሰዎች" እንዳሉ ገልጸው፣ "ለተፈናቃዮቹ የሚደረገው ምግብ እና ሌሎች መሰረታዊ አቅርቦቶች እየተሻሻለ መምጣቱን" ለኮሚሽኑ ቡድን አስረድተዋል።

የዳንሻ ወረዳ የትግራይ ብሔር ተወላጆች የፀጥታ ችግር እንደተሻሻለ ይናገራሉ። ሆኖም ብሔርን መሰረት ያደረገ ጥቃት ይደርስብናል የሚል ፍራቻ እንዳለና በተለይም "በማይካድራ በተፈጸመው ኢ-ሰብአዊ ጭፍጨፋ መነሻነት የበቀል ጥቃት ይደርስብናል" የሚል ስጋት እንዳደረባቸው ገልጸዋል። ተመሳሳይ ስጋት ያደረባቸው የተወሰኑ የአካባቢው ነዋሪዎችም ወደ ሌሎች አካባቢዎች መሄዳቸውን አክለው አስረድተዋል።

የዳንሻ ወረዳ ጊዜያዊ አስተባባሪ በአካባቢው የሚኖሩ የትግራይ ብሔር ተወላጆች በሰላማዊ ሁኔታ እንደሚኖሩ ገልጸው፣ "ስጋት አለብን" በማለት ጥያቄ ላቀረቡ የብሔሩ ተወላጆች "ትራንስፖርት አዘጋጅተው ወደሚፈልጉበት ቦታ የተወሰዱበት ሁኔታ ነበር" ብለዋል። "አሁን ያለውን ሁኔታ በተመለከተ በወረዳው የሕዝብ ለሕዝብ መድረክ በመፍጠር የነበረውን ክስተት እና ጉዳት እርስ በርስ በመጠፋፋት መቅረፍ እንደማይቻል በመተማማን፣ ሁሉም ሰዎች በሰላምና በመከባበር ኑሯቸውን እንዲቀጥሉ ወይይት አድርገናል። ይሁንና በወረዳው የሕወሓት ባለሥልጣናት አሁንም ጥቃት ሊያደርሱ እንደሚችሉ እና በተለይም በአማራ እና በትግራይ ብሔር ተወላጆች መካከል መከፋፈልን ያመጡብናል የሚል ስጋት አለብን" ሲሉ ያስረዳሉ።

የዳንሻ ከተማ ወደ መደበኛ እንቅስቃሴ መግባቱንና አንጻራዊ ሰላማዊ ሁኔታ መፈጠሩን ቡድኑ መመልከት ቢችልም፣ በአንጻሩ የብሔር ተኮር ጥቃት ስጋትና ፍርኃት ያደረባቸው የተወሰኑ የትግራይ ብሔር ተወላጅ የወረዳው ነዋሪዎች እንደነበሩ የምርመራ ቡድኑ ለመታዘብ ችሏል።

ኢሰመኮ በታኅሣሥ ወር ባደረገው ጉብኝት በዳንሻ ወረዳ የሚገኙ የጤና፣ የትራንስፖርት፣ የስልክ፣ የንግድ ቦታዎች፣ የባንክ አገልግሎቶች (በዳሽን ባንክ እና በአባይ ባንክ) ወደ መደበኛ አገልግሎት ተመልሰው አይቷል (እንዲሁም በዚህ ሪፖርት ዝግጅት ወቅት አቢሲንያ ባንክ እና አንበሳ ባንክ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውንም ተረድቷል።) ይህንኑ ከወረዳው ጊዜያዊ አስተባባሪ እና ከነዋሪዎች እንዲሁም የኢሰመኮ ምርመራ ቡድን ተዘዋውሮ ባደረገው ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል። በወቅቱ ያልተሰበሰቡ የማሽላ፣ የጥጥ፣ የሰሊጥ እና መሰል አዝመራዎች ህብረተሰቡን በማስተባበር መሰብሰባቸውን እና ከብክነት ለማዳን መቻሉን አስተዳደሩ እና ነዋሪዎች አስረድተዋል።

ይሁንና በዚህ ሪፖርት ዝግጅት ወቅት የመብራት፣ የውሃና የትምህርት መሰረታዊ አገልግሎቶች ወደ መደበኛ ሁኔታቸው አልተመለሱም። የዳንሻ ወረዳ ጊዜያዊ አስተባባሪ "የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ባለመጀመሩ ምክንያት፣ ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር በመበራከቱ፣ አዲሱ የብር ኖት በአካባቢው አገልግሎት ባለመዋሉ እና በዚሁ ምክንያት የቀድሞው ብር ኖቶች አሁንም ጥቅም ላይ እየዋሉ በመሆናቸው ስራውን ለመጀመር መቸገሩን" ገልጸው "በአሁኑ ወቅት ግን ባንኩ አገልግሎቱን መልሶ ለማስጀመር እንቅስቃሴ ላይ ነው " በማለት አስረድተዋል።

ኮሚሽኑ በዳንሻ በነበረባቸው ቀናት፣ የዳንሻ ጤና ጣቢያ ችግሮች አልተፈቱም ነበር። ጤና ጣቢያው ከጥቅምት ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ለሰራተኞች የወር ደመወዝ አልከፈለም፣ የተወሰኑ ሰራተኞች አካባቢውን ለቅቀው ሄደዋል፣ እንዲሁም የጤና ጣቢያው አምቡላንሶች አገልግሎት እየሰጡ ባለመሆናቸው ከሌላ ወረዳ እየተዋሰ ለመስራት ተገዷል። የመንግስት ተቋማት ሙሉ በሙሉ ወደስራ ስላልተመለሱ ወረዳው ግዥ ለመፈጸም በመቸገሩ፣ የመድኃኒት እጥረት ያጋጥማል የሚል ስጋት ነበረው። በተለይም የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት አለመኖሩ መድኃኒቶችን እና የህክምና መሳሪያዎችን ለብልሽት ዳርጓል።

## ቢሶበር እና ኡላጋ መንደሮች

ቢሶበር እና ኡላጋ መንደሮች በጨርጨር ወረዳ የሚገኙና የአማራ፣ የትግራይ፣ የኦሮሞ እና የአፋር ክልል ተወላጆች የሚኖሩባቸው አነስተኛ ከተሞች ናቸው። ወረዳው በራያ አዘቦ ወረዳ የሚገኝ አካባቢ ሲሆን፣ ጨርጨር ከተማ የትግራይ እና የአፋር ክልሎችን የሚያዋስነው ጠረፍ አካባቢ ይገኛል። የጨርጨር ወረዳ መቀመጫ ጨርጨር ከተማ ስትሆን፣ ከአላማጣ በስተሰሜን ምስራቅ ወደ 50 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ትገኛለች። በአሁኑ ወቅት የጨርጨር ከተማ ሕዝብ ቁጥር ወደ 30 ሺህ እንደሚደርስ ሲገመት፣ የቢሶበር መንደር እና ኡላጋ ቀበሌ አጠቃላይ ሕዝብ ብዛት ከ3000 እንደማይበልጥ ይገመታል።

ከግንቦት ወር 2012 ዓ.ም. ጀምሮ በወቅቱ በሥልጣን ላይ የነበረው የሕወሓት ልዩ ኃይል የኮሮና በሽታን ለመከላከል እና በአፋር ክልል አድርገው ከጂቡቲ ወደ ትግራይ የሚገቡ ሰዎችን ለመቆጣጠር በሚል ምክንያት በቢሶበር መንደር በሚገኘው የኡላጋ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ መስፈሩን፤ ሆኖም ግን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ምሽግ ሲቆፍርና ለጦርነት ዝግጅት ሲያደርግ የቆየ መሆኑን ነዋሪዎች ይናገራሉ፤ የኮሚሽኑ የምርመራ ቡድንም ይህንኑ በምልከታ ለማረጋገጥ ችሏል።

ኅዳር 5 ቀን 2013 ዓ.ም. ከንጋቱ 11:00 ሰዓት ላይ በትግራይ ልዩ ኃይል እና በፌዴራል መከላከያ ሠራዊት መካከል የተጀመረውና የከባድ መሳሪያ ድምጽ ይሰማ የነበረበት ውጊያ ለሦስት ቀናት ቆይቷል። ምስክሮች ለኮሚሽኑ የምርመራ ቡድን እንዳስረዱት የሕወሓት ልዩ ኃይሎች ሲቪል ልብስ በመልበስና በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ጭምር በመመሸግ ተዋግተዋል። ነዋሪዎቹ የልዩ ኃይሉ አባላት ከመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ሆነው ጥይት ሲተኩሱ የነበረ መሆኑን ገልጸው በጥይት የተበሱ መኖሪያ ቤቶችን ለኮሚሽኑ የምርመራ ቡድን አሳይተዋል።

የተኩስ ልውውጡ እያየለ ሲመጣ ነዋሪዎች ቤትና ንብረታቸውን ጥለው ወደ ተለያዩ አጎራባች መንደሮች በተለይም ቡታ፣መፈርታ እና ያሎ ወደተባሉ አካባቢዎች መሸሽ ጀመሩ። በመንገድ ላይ በጥይት ተመትተው የአካል ጉዳት የደረሰባቸው እና መሮጥ አቅቷቸው የተቸገሩ ሰዎች እንዳጋጠሟቸው ተጎጂዎች ያስረዳሉ።

በቢሶበርና በኡላጋ መንደሮች በነበረው ውጊያ በአጠቃላይ 31 ሲቪል ሰዎች የሞቱ ሲሆን አብዛኛዎቹ ሰዎች ለሶስት ቀን በዘለቀው የተኩስ ልውውጥ በድንገት በጥይት ተመትተው የሞቱና የተወሰኑ ሰዎች ደግሞ በውጊያው ተሳታፊ በነበሩ ወታደሮችና ለጊዜው ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች በተፈጸመ ጥቃት የተገደሉ መሆናቸውን ነዋሪዎች አስረድተዋል።

በተለይ በቢሶበር መንደር 3 ሴቶች እና 24 ወንዶች መሞታቸውን፣ እንዲሁም 9 ወንዶች የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው ኮሚሽኑ የተረዳ ሲሆን ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ አባት፣ እናትና ልጅን ጨምሮ ሞተዋል። በቢሶበር መንደር የሞቱት ሰዎች ዝናቤ ገላኔ እና አበራ ገላኔ፤ ኢያሱ ባራኪ፣ ጥጋቡ አብረሃ፣ ኅበዜ ጥጋቡ እና ረዳ ጥጋቡ (አባትና ልጆች)፤ ታደለ ቦጋለ፣ ጠቋሬ አረጋ እና ገብሬ ታደለ (አባት፣እናት እና ልጅ)፤ ተስፋዬ አበራ፣ ኮሌ ሲሳይ፣ ጥጋቡ አበራ እና አበበ ንግሱ(ጎረቤታማቾች)፤ ብርሃኑ ሀገዞም፣ ጥጋቡ ሀጎስ እና ምስጋን አበበ (የአንድ ሰፈር ነዋሪዎች)፤ አስማረ አስፌ፤ ሰለሞን ዘገየ፤ ሰርጌ ጣውያ፤ ሻምበል ካሳ እና ክብሮም ወ/ስላሴ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም 9 ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

በኡላጋ መንደር ጎብየ ረታ እና አዲና ወዳጆ የሚባሉ ባለትዳሮች፣ እንዲሁም ደርቤ ገዛኢ እና አዳነ ፋጂ የሚባሉ ሰዎች መሞታቸውን ከነዋሪዎች ለመረዳት ተችሏል።

ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የቢሶበር ነዋሪዎች በስም ከተዘረዘሩት ሲቪል ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ በውጊያው ወቅት በነበረው ተኩስ ልውውጥ የሞቱ መሆናቸውን ያስረዳሉ። ይሁንና ለምሳሌ አቶ ተስፋዬ አበራ የተባሉት የቢሶበር ነዋሪ የነበሩ ሚች ታርደው የሞቱ መሆናቸውን አሬሳውን በማየት መረዳት ቢችሉም፣ ማን እንደገደላቸው አለማወቃቸውን የሚቹን ቀብር የፈጸሙት ምስክሮች ገልጸዋል። በተጨማሪም አንድ እናት፣ የባለቤታቸውን እና የልጃቸውን አሟሟት ለኮሚሽኑ በኃዘን ከገለጹ በኋላ የተወሰኑ የመከላከያ ሠራዊት አባላት "ለጠላት መረጃ ታቀብላለህ" በሚል ያላግባብ

እንደገደለባቸው ይናገራሉ። አንድ ሌላ የቢሶበር ነዋሪም አካል ጉዳተኛ ልጃቸው በተመሳሳይ መልኩ እንደተገደለ ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። በመሸሸ ላይ ወይም እቤት ውስጥ እያሉ "መረጃ ለሕወሓት ታቀብላለህ" በሚል መደብደባቸውን የሚገልጹ ሰዎችን ኮሚሽኑ አነጋግሯል።

በቢሶበር የሞቱትን ሰዎች መቅበር የተቻለው ከአምስት ቀናት በኋላ ወይም በኅዳር 10 ቀን 2013 ዓ.ም. የመከላከያ ሠራዊት ወደ አካባቢው መመለስና ቀብር ማስፈጸም የሚቻል መሆኑን ሲገልጽ መሆኑን ተጎጂዎችና የተጎጂዎች ቤተሰቦች አስረድተዋል። ከሟቾች መካከል አንዳንዳዶቹ መሞታቸው የታወቀው በዚሁ ወቅት እንደሆነና፣ የአንዳንድ አስከሬኖች ሁኔታ ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ የሚፈቅድ ባለመሆኑ በወደቁበት በቤታቸው በር ላይ ለመቅበር መገደዳቸውን ነዋሪዎች አክለው ገልጸዋል። የኮሚሽኑ የምርመራ ቡድን በተገለጹት ቦታዎች ላይ የሚገኙ መቃብሮችን ተመልክቷል።

ወደሌላ አካባቢዎች በሚደረገው ሽሽት ወቅት ሁለት ነፍሰጡር ሴቶች መንገድ ላይ ሲንገላቱ የነበረ መሆኑን ነዋሪዎቹ ያስረዳሉ። አንደኛዋ እናት መንገድ ላይ ለመውለድ በመገደዳቸው ልጃቸው እንደሞተባቸው፣ ሁለተኛዋ እናት ደግሞ ከከፍተኛ ስቃይ በኋላ ወደቤታቸው ተመልሰው መውለዳቸውን ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ የጨርጨር ወረዳን በጊዜያዊነት የሚያስተዳድሩትን የኮማንድ ፖስት ተወካዮች፣ እንዲሁም የጊዜያዊ አስተዳደርና የፀጥታ ኃይል አባሎችን ያነጋገረ ቢሆንም በቦታው የተሾሙት ከኅዳር 8 ቀን 2013 ዓ.ም. በኋላ በመሆኑ አስቀድሞ ስለተፈጠረው ሁኔታ የተሟላ መረጃ የላቸውም። ይልቁንም ነዋሪዎች በአሁኑ ወቅት ለአካባቢው ጥበቃ በማድረግ ላይ የሚገኘው የፀጥታ ኃይል በወቅቱ አካባቢው ላይ ስለተፈጠረው ሁኔታ መረጃ ሲደርሰው ከፍተኛ ድንጋጤና ኃዘን እንደተሰማው ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ ባደረገው ምልከታ በቢሶበር መንደር፣ 104 ቤቶች ሙሉ በሙሉ፣ የተወሰኑ ተጨማሪ ቤቶች ደግሞ በከፊል በእሳት ቃጠሎ እና በጦርነቱ ውጤት መውደማቸውን ለማረጋገጥ ችሏል። ቢሶበር የሚገኘው የኡላጋ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት በከፊል በከባድ መሳሪያ ተመቶ የተቃጠለ መሆኑንና የኡላጋ መንደር ጤና ጣቢያ ከባድ ውድመት ደርሶበት አገልግሎት መስጠት ማቆሙን ተመልክቷል።

እንዲሁም የግለሰቦች ንብረት ተዘርፏል፣ በእሳት ወድሟል። ለምሳሌ አንድ ተጎጂ 15 በጎች እና በጎተራ የተቀመጠ እህላቸው ሙሉ በሙሉ እንደተቃጠለባቸው ገልጸዋል። በቢሶበር የተለያዩ የንግድ ሱቆች እና መኖሪያ ቤቶች ተዘርፈዋል። ነዋሪዎች ዝርፊያው እንደተከሰተ ያዩት ከሸሹባቸው አካባቢዎች ሲመለሱ መሆኑና ዘራፊዎቹ ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ ሰዎች መሆናቸውን እንደሚገምቱ አስረድተዋል።

## ተጎጂዎችና ተፈናቃዮች የሚገኙበት ሁኔታ

በትግራይ ክልል ከሁለት ወራት በላይ በዘለቀው ጦርነት ምክንያት 2.2 ሚልየን ሰዎች አስቸኳይ የሰብአዊ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው በክልሉ የተቋቋመው ጊዜያዊ አስተዳደር ያካሄደውን ዳሰሳ ጠቅሶ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል። በትግራይ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት ፍላጎት እጅግ አንገብጋቢ በሚባል ደረጃ ላይ መድረሱን ኮሚሽኑ በመቀሌ ያነጋገራቸው የሲቪል አመራሮች፣ የወታደራዊ አመራሮች፣ የሰብአዊ እርዳታ ተቋማት እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ገልጸዋል።

የኮሚሽኑ ባለሞያዎች በመቐለ ከተማ የተጠለሉ እና ግጭቱን በመሸሽ ከተለያዩ ዞኖች አድካሚ የእግር ጉዞዎችን በማድረግ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተጠለሉ ሰዎችን መመልከት ችሏል። አብዛኞቹ ተፈናቃዮች ጦርነቱ ከተጀመረ እና ጉዳት መድረስ ከጀመረ በኋላ ወደ መቐለ የመጡ ሲሆኑ የተወሰኑት ተፈናቃዮች የነፍስ አድን እርዳታዎችን አግኝተዋል። ቢሆንም አሁንም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተፈናቃዮች ከህብረተሰቡ በሚዋጣ ድጋፍ እየተረዱ ይገኛሉ። ከእነዚህ ተፈናቃዮች ውስጥ አብዛኞቹ ለቀው ወደመጡት ቀያቸው መመለስ ቢፈልጉም ጥለውት በመጡት አካባቢ ያለው አጠቃላይ የሰላም ሁኔታ ግን ያሳስባቸዋል። በተለይም በክልሉ በተከሰተው የሰላም መደፍረስ ከእስር የወጡ የተወሰኑ ሰዎች በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ወንጀል እየፈጸሙ እንደሆነ ይነገራል። በሌላ በኩል የተወሰኑት ተፈናቃዮች ጥለውት የመጡት ቤታቸው፣ ከብቶቻቸው፣ እህላቸው እና ያልተሰበሰበ

አዝመራቸው መዘረፉን ወይም መቃጠሉን ተናግረው መቋቋሚያ ሳያገኙ ወደመጡበት መመለስ እንደማይችሉ ያስረዳሉ። ከመሰረተ ልማቶች አንጻር በትግራይ ክልል በየደረጃው በጦርነቱ የተጎዱ መሰረተ ልማቶች ጥገና እየተደረገላቸው ቢሆንም፣ በበርካታ የክልሉ አካባቢዎች የመብራት ኃይል አቅርቦት ባለመኖሩ ምክንያት  የስልክ፣ የጤና ተቋማት፣ የእህል ወፍጮዎች ብሎም የፋይናንስ ተቋማት ወደ ስራ መግባት አልቻሉም። የስልክ አገልግሎት በሌለባቸው በተለይም በምሥራቅ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ማዕከላዊ ዞኖች የሚኖሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተጠፋፍተዋል።

በአማራ ብሔራዊ ክልል አደጋ መከላከልና ምግብ  ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት  የማዕከላዊ ጎንደር ዞን አደጋ መካላከልና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በሰነድ ማስረጃ ጭምር ከተለያዩ የትግራይ ክልል አካባቢዎች ስለተፈናቀሉ ሰዎች ብዛትና አጠቃላይ የሰብአዊ እርዳታ ፍላጎት የተለያዩ መረጃዎች ለኮሚሽኑ ሰጥቷል። ለምሳሌ 73 ሺህ 783 ያክል ከትግራይ ክልል የተፈናቀሉ ሰዎች፣በዳንሻ፣ በአዲረመጥ፣ በሃከር፣ በሁመራ እና በማይካድራ የሚገኙና መተዳደሪያ ገቢያቸውን በጦርነቱ ምክንያት ያጡ መሆናቸውን በመግለጽ፣ በተለይ የምግብ እርዳታ እንደሚሹ ያስረዳል። በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገኙና በቀድሞው የሕወሓት አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች የነበሩ 2 ሺህ 135 ሰዎች በከተማ ንጉሥ እና በሌሎች አካባቢዎች እንደሚገኙ ተገልጿል።

ከጥሬ ገንዘብ እጥረት ጋር ተዳምሮ የምግብ እጥረት እንዲባባስ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ የአካባቢው ማኅበረሰብ ከዚህ ቀደም “በግዴታ የገንዘብ ቁጠባ የሚያስቀምጡት በደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ ስለነበር ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ጥሬ ገንዘብ በዚህ ተቋም የሚገኝ መሆኑና፣ የቀድሞው ትግራይ ክልል አስተዳደርና ልዩ ኃይሎች ከተማውን ለቅቀው ሲወጡ አካባቢውን ዘርፈው፣ ማስረጃዎችን  አጥፍተው በመሄዳቸው የግለሰቦችን ተቀማጭ ሂሳብ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅና ለግለሰቦች ገንዘባቸውን መመለስ አለመቻሉ” መሆኑን የዳንሻ ጊዜያዊ አስተዳደር ገልጿል። ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ከስራ ገበታቸው የተፈናቀሉ ሰዎችም ይህንኑ አረጋግጠዋል።

የኮሚሽኑ ምርመራ ቡድን በዳንሻ ከተማ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት እና በጎንደር ከተማ፣ በአዘዞ ቀበሮ ሜዳ፣ በቀበሌ 19 የተጠለሉ ተፈናቃዮችን ድንገተኛ ምልከታ በማድረግ ጎብኝቷል። ከተለያዩ የመንግስት አካላት እንደተገለጸው 3,136 የሚሆኑ ተፈናቃዮች መኖራቸውን ሰነዶችን በማየት ጭምር ለማረጋገጥ ተችሏል።

በጎንደር ከተማ የሚገኙ 648 የትግራይ ክልል ተፈናቃዮች የምርመራ ቡድኑ በታኅሣሥ ወር ምልከታውን እስካደረገበት ወቅት ድረስ፣ እርዳታ የሚያገኙት በአብዛኛው ከጎንደር ከተማ ነዋሪ ነው። የከተማዋ ነዋሪዎችና የመንግስት ሰራተኞች በማኅበር እና በሰፈር በመደራጀት  እንጀራ፣ በርበሬና ሽሮ እንዳቀረቡላቸው ተፈናቃዮቹ ገልጸዋል። በተለይም በዳንሻ እና በሁመራ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ወደመደበኛ ስራቸው አለመመለስ፣ በጦርነቱ ምክንያት የተባባሰውን የምግብ ምርቶች እጥረት፣ የምግብ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምርና ከነዋሪዎች አቅምና ወቅታዊ ሁኔታ በላይ እንዲሆን አድርጎታል። ሁኔታው የተፈናቃዮችንና አጠቃላይ የአካባቢዎቹን ሰብአዊ መብቶች ጥበቃ አሳሳቢ  የሚያደርግ ነው።

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች  የተወሰነ ዱቄት፣  ዘይት እና የመኝታ ፍራሽ  በእርዳታ መስጠቱን”፤ እንዲሁም  በሳምንት ሦስት ቀን  የህክምና አገልግሎት እንደሚሰጣቸው” ተፈናቃዮቹ አስረድተዋል። በተጨማሪም   ነፍሰ-ጡሮችን፣ የአዕምሮ ሕመምተኞችን   እና ሌሎች ከፍተኛ ህመም ያለባቸውን ተፈናቃዮች ወደ ጎንደር ሆስፒታል በመላክ  ህክምና እንዲሰጣቸው መደረጉን ለመረዳት ተችሏል።

በቢሶበር ቤታቸው የተቃጠለባቸው ሰዎች በመንደሩ ውስጥ  ጊዜያዊ መጠለያዎች ሰርተው፣ የተወሰኑት ተከራይተው፣ሌሎች ደግሞ በሌሎች ሰዎች ቤት  ተጠግተው ይገኛሉ። ለኡላጋ መንደር ተፈናቃዮች መንግስት  የተወሰነ ስንዴ እና ገንዘብ ማከፋፈሉንና ዓለምአቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች  የተወሰነ ሽራዎችን፣ ጀሪካኖችን፣ ብርድ ልብሶችንና ልብስ ማጠቢያዎችን እንዲሁም ምግብ ለማብሰልና ለመመገብ የሚያገለግሉ የቤት ቁሳቁሶች መስጠቱን የምርመራ ቡድኑ ከተፈናቃዮቹ ተረድቷል።

## ምክረ ሃሳብ

- በሁመራ እና በዳንሻም ሆነ በቢሶበር እና ኡላጋ የሚኖረው ህብረተሰብ የደኅንነት ስጋት አልተወገደም። በሁመራ እና በዳንሻ በሚኖሩ የትግራይ ብሔር ተወላጆች ላይ ብሔር ተኮር መንገላታቶች እየደረሱ ነው። የፍትሕ አካላት ወደ መደበኛ ስራቸው አለመመለሳቸው እነዚህን ስጋቶች የሚያባብስና ተጨማሪ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት የሚያስከትል በመሆኑ የፌዴራል መንግስት በአፋጣኝ የአካባቢውን ፀጥታ እና የህብረተሰቡን ደኅንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።
- በዚህ ሪፖርት በተካተቱ አካባቢዎች በተወሰኑ የፀጥታ ኃይል አባሎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተገቢው ምርመራ ተደርጎ የአጥፊዎቹ ተጠያቂነት ሊረጋገጥ ይገባል፣
- ለነዋሪዎችና ተፈናቃዮች የመጀመሪያ ዙር እርዳታ መደረጉ አበረታች ቢሆንም በነዋሪዎቹና በአካባቢዎቹ ላይ ከደረሰው ጉዳት አንጻር ከፍተኛ የሰብአዊ እርዳታ የሚያስፈልግ በመሆኑ መንግስትና ሰብአዊ ድጋፍ የሚያቀርቡ ዓለምአቀፍ ተቋማትና ሁሉም ኢትዮጵያውያን ርብርብ እንዲያደርጉ ኢሰመኮ ጥሪ ያቀርባል። በተለይም ግጭት ባልቆመባቸውና የፀጥታ ሁኔታው አስጊ በሆነባቸው የክልሉ አካባቢዎች ለሲቪል ሰዎች እርዳታ ለማቅረብ የመከላከያ ሠራዊቱን ድጋፍ ጨምሮ፣ አስፈላጊው ጥረት መደረግ አለበት።